የሰ/መ/ቁ. 25765

ጥቅምት 07 ቀን 2000

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ኃይለሚካኤል ይህደጎ

ተጠሪ፡- ግርማ አየለ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል፡፡

ፍ ር ድ

የዚህ መዝገብ ክርክር የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ ለልሰና ሥራ በአመልካች ተቀጥሬ እየሠራሁ ባለሁበት አመልካቹ ያለጥፋት የሥራ ውሌን ስላቋረጠ ወደ ሥራ ሊመልሰኝ ይገባል ይህ ካልሆነም የሥራ ስንብት፣ የካሣና ሌሎች ክፍያዎች ሊከፈለኝ ይገባል ሲል ክስ መስርቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪው በግል ሕንፃዬ ላይ ይሠራ የነበረው ጊዜያዊ ሥራ ነው፤ ሥራው በመጠናቀቁ ነው የተሠናበተው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ተጠሪ ከሥራ የተሰናበተው ሥራው በማለቁ ምክንያት መሆኑን አመልካች አላስረዳም፤ በማለት ተጠሪ የጠየቃቸው ክፍያዎችን ሊያገኝ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሠርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝቶ ለዚህ ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ ተጠሪ የተቀጠረው ለግል ቤቴ የልሰና ሥራ ለአጭር ጊዜ ነው፤ አንድ ወር እንኳን መሥራቱን ባላስረዳበት ሁኔታ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ያላግባብ ነው ተብሎ የተወሰነብኝ ውሣኔ ሊሻር ይገባል በማለት ነው፡፡ ተጠሪ የተቀጠረው ለተወሰነ ሥራ መሆን ያለመሆኑን ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክር ተሠምቷል፡፡

ተጠሪ ለልሠና ሥራ የተቀጠረ መሆኑ የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ላይ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የተቀጠረው አመልካች ለድርጅት ሥራው በሚያስገነባው ሕንፃ ላይ መሆኑን በውሣኔው ጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም ተጠሪው በቋሚ ሥራ አለመቀጠሩንም በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የሥራ ውል ባሕርይ፣ ሲገለጽ ጠቅሶታል፡፡

የሥራ ውል ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሠሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሠሪው ለመሥራት የሚደረግ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 4/1/ ይደነግጋል፡፡

ተጠሪ የተቀጠረው አመልካች ያሠራ ለነበረው ቤት የልሰና ሥራ እንዲሠራ ነው፡፡ ቤቱን የመለሰን ሥራ ሲያበቃ የሥራ ውሉም ያበቃል ማለት ነው (አንቀጽ 10/1/ሀ/) ፡፡ በሁለቱ መካከል ይህ ውለታ መኖሩ እየታወቀ ሥራው በማለቁ ምክንያት ተጠሪ ስለመሠናበቱ አመልካች አላስረዳም በማለት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ከላይ በሕጉ ላይ እንደተገለፀው የሥራ ውል ለተወሰነ ሥራ ሊያደርግ እንደሚችል የተደነገገውን ያላገናዘበ ነው፡፡

በሌላ በኩል የሥራ ስንብት ክፍያና ካሣ የሚከፍለው የሙከራ ጊዜውን ለጨረሰና በአዋጁ አንቀጽ 39 ሥር በተመለከቱት ምክንያቶች የሥራ ውሉ ለተቋረጠበት ሠራተኛ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ግን የተጠሪው የሥራ ውል ለተወሰነ ሥራ የተደረገና ሥራው በማለቁ ውሉ የተቋረጠ በመሆኑ የስንብትና የካሣ ክፍያ ይከፈለው መባሉ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ተወስኗል፡፡